መመሪያ.ቁ 731/2013

ቁጥር ሀ1-8/78/00/20/125

ቀን 29/8/2006

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማት ፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Urban Development
Housing & Construction

ለፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የስትሪንግ ኮሚቴ ውሳኔዎችን ስለማስፈፀም</u>

የሴቶች ኢንተርፕርነርሸፕ ልማት ፕሮጀክት ስትሪንግ ኮሚቴው ሚያዝያ 01 ቀን 2006 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ በልዩ ልዩ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔዎችን ማሳለፉና ማፅደቁ ይታወሳል፡፡ በመሆኑም

1ኛ. ለመጨረሻ ጊዜ ታርሞና ተስተካክሎ የቀረበውና በዕለቱ የፀደቀው የሴቶች ኢንተርፕረነርሸፕ ልማት ፕሮጀክት የድጋፍና የአሰራር መመርያ ስራ ላይ እንዲውል የተወሰነ በመሆኑ ለኮሚቴ አባላቱ እንዲደርሳቸው እንዲደረግ፣

2ኛ. የፕሮጀክቱ ሠራተኞች ደመወዝ፣ ጥቅማ ጥቅሞችና አበልን በተመለከተ ከሚያዝያ 01/2006 ዓ.ም ጀምሮ በቃለ ጉባኤው ላይ (በሰንጠረዥ) በተመለከተው ውሳኔ መሰረት ተግባራዊ እንዲደረግ የስትሪንግ ኮሚቴውን የውሳኔ ቃለ ጉባኤ በዚህ ደብዳቤ አባሪነት የተላከ መሆኑን አስታውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ ተ/ማርያም
ሚኒስትር

<u>ግልባጭ</u>

- ለከተማ ልማት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ ጽ/ቤት
- ለሕግ መምሪያ
  <u>ከ/ል/ቤ/ኮ/ሚ</u>
- ለሴቶች ኢንተርፕርነርሸፕ ልማት ፕሮጀክት
  ጥ/አ/ኢ/ል/ኤ
  <u>አዲስ አበባ</u>

# በከተማ ልማት፣ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

## የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የሴቶች ኢንተርፕሪነርሽፕ ልማት ፕሮጀክት የድጋፍና የአሠራር መመሪያ ቁጥር 731/2013

ሚያዝያ/2006
አዲስ አበባ

## መግቢያ

በኢትዮጵያ መንግሥትና በዓለም ባንክ መካከል በተደረሰ ስምምነት መሰረት የሴቶችን ተጠቃሚነትን ለማሳደግ የሴቶች ኢንተርፐሪነርሽፕ ልማትፕሮጀክት (Women Entrepreneurship Development Project) ተዘጋጅቶ ከባንኩ ጋር የ50 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የብድር ስምምነት ተፈርሟል፡፡

በመሆኑም የፕሮጀክቱ የዝግጅት ምዕራፍ ሥራዎችን በማጠናቀቅ የፕሮጀክቱ ባለቤት በሆነው በከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴርና ሚኒስቴር መ/ቤቱን ወክሎ ፕሮጀክቱን በሚያስፈጽመው የፌደራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች ጋር ተቀናጅቶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

ከዚህ አንጻር የፕሮጀክቱን ዓላማ ለማስፈፀምና የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በፀደቀው የፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ሠነድ መሠረት ስራውን የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ካውንስል የሚከታተለው ሲሆን የሚኒስቴር መ/ቤቱም ከፕሮጀክቱ ፈጻሚ መ/ቤቶች ጋር አብሮ ለመስራትና ለማስተባበር የተደረጉ ጥረቶችን ማጠናከር አስፈልጓል፡፡

ይህም በመሆኑ ፕሮጀክቱ ለተጠቃሚዎቹ በወቅቱ ተደራሽ ለማድረግና የታለመለትን አላማ ማሳካት እንዲቻል በእድገት ተኮር የስራ ዘርፎች የተሰማሩትን ሴት ኢንተርፕረነሮች ገቢ ማሳደግና ስራ ፈጣሪ ለማድረግ የሚያስችሉ የቴክኒዮሎጂ ፣የፋይናንስና የገበያ እንዲሁም የመስሪያ ቦታ አቅርቦት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

አቅርቦቶችን ከማጠናከርና ተደራሽ ከማድረግ ባሻገር በተለይ በምርት ተግባር ላይ (Manufacturing) ሥራ ላይ የተሰማሩትን የብድር ተጠቃሚ በማድረግ፣በማሰልጠን ፣ተከታትሎ ለውጤት በማብቃት የጎላ ተሳትፎና አስተዋጽኦ ያበረከቱ ተቋማት እንዲሁም ለከፍተኛ ውጤት የበቁት ሴት ኢንተርፕረነሮች የሚበረታቱበትና የሚሸለሙበት አግባብ ይመቻቻል፡፡

ይህም በመሆኑ የኢንተርፕራይዞቹን ጥረትና የአስፈጻሚዎችን አስተዋጽኦ ለውጤት እንዲበቃ በሚያስችል መልኩ የተደራጀና የተቀናጀ ድጋፍና አመራር መስጠት ተገቢ በመሆኑ፣ በየደረጃው ያሉት አካላትም ለዘርፉ የሚሰጡትን ድጋፍ ለማስተባበርና ለማስፈጸም እንዲያስችል በሁለት እርከኖ[illegible] ኮሚቴዎች በዚህ መመርያ ተዋቅረዋል፡፡ ኮሚቴዎቹም

...Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development Housing & Construction

1ኛ/ ስትሪንግ ኮሚቴ (Steering Committee) የበላይ አመራሮች የሚገኙበት፤

2ኛ/ አስተግባሪ ኮሚቴ (Operational Committee) የፈጻሚ መ/ቤቶች ዳይሬክተሮችና ከፍተኛ አመራሮች አባል የሚሆኑበት ነው።

ኮሚቴዎቹ በዚህ መመርያ ከላይ የተጠቀሰውን አላማ በማስፈጸም በኩል የእያንዳንዱ ኮሚቴ የስራ ድርሻና ሀላፊነት ተለይቷል፤ በተለይ የፕሮጀክቱ ተግባራት ከፌደራል እስከ አንድ ማእከል አገልግሎት ድረስ በተቀናጀና ለውጤት በሚበቃ መልኩ በመፈጸም ላይ መሆኑን ለማረጋገጥ አፈጻጸሙን ለመገምገምና ክትትል ለማድረግ በሚያግዝ መልክ ሲሆን፤ መመርያው የፕሮጀክቱን የሥራ ውጤት የሚለካበት፡ እንዲሁም እገዛ የሚደርግበትና አመራርና አቅጣጫ የሚሰጥበት ሆኖ ተዘጋጅቷል።

በተጨማሪም በሥራ ላይ ላሉት የፕሮጀክቱ ሠራተኞችና ድጋፍ ሰጪ አካላት የማበረታቻ ሥርዓት በዓይነትና በመጠን እንዲዘጋጅ ተደርጓል። በተለይም ፕሮጀክቱ የታለመለትን ግብ ከማሟላት በሻገር ለሌሎች ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች አርአያ የሚሆንበት፤ ተሞክሮ የሚያካፍል እንዲሆንና ፕሮጀክቱን በማስፋት ለመላው የሀገሪቱ ኢንተርፕሪነር ሴቶች ተደራሽ ለማድረግ እንዲያግዝ በሚረዳ መልኩ ለመምራት እንዲያስችል ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አጭር ርእስ

ይህ የአፈጻጸም መመሪያ የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የሴቶች ኢንተርፕረነርሽፕ ልማት ፕሮጀክት የድጋፍና የአሠራር መመሪያ ቁጥር 731/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) «ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር» ማለት እንደቅደም ተከተሉ የከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

2) ‹‹ፕሮጀክት›› በእድገት ተኮር የሥራ ዘርፎች ለተሰማሩ ሴት ኢንተርፐረነሮች የገቢ፤የክህሎትና የሥራ እድል ፈጠራ ለማሻሻልና ለማሳደግ የብድርና የክህሎት አገልግሎት የሚያመቻችና ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች ጋር በመተባበር በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በሁለት የቻርተር ከተሞችና በአራት ክልል ዋና ከተሞች የሚተገበር የልማት አደረጃጀት ነው፡፡

3) «የአንድ ማዕከል አገልግሎት» ማለት የዚህ ፕሮጀክት ተጠቃሚ የሆኑ የሴት ኢንተርፐረነር ኢንተርፕራይዞችን ሕጋዊነት ለማስፈን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የሚሰጡ አገልግሎቶችንና መንግሥታዊ ድጋፎችን በተቀናጀ መልኩ በአንድ ሥፍራ የሚሰጥበት አደረጃጀት ነው፡፡

4) «ክልል» ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47/1 የተመለከቱትን ክልሎች ማለት ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል የአዲስ አበባና የድሬዳዋ አስተዳደርንም ይጨምራል፡፡

5) «የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ» ማለት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በበላይነት የሚመራ የፌዴራል አካል ነው፡፡

6) «የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች» ማለት የሴት ኢንተርፕሬነሮች ያለባቸውን የቴክኖሎጂ፣ የፋይናንስ ፤የኢኮኖሚና የገበያ መሠረተ ልማትን ግንዛቤና ክህሎት የሚያስጨብጥና ክፍተት በመለየት ችግር ፈቺ ሥልጠናዎችን በመስጠትና በማብቃት በፕሮጀክቱ ሥራ እንዲሳተፉ የተመረጡ ኮሌጆች ናቸው፡፡

5) «አነስተኛ የብድርና ቁጠባ ተቋማት» ማለት በፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ለሆኑ የሴቶች ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ፣ የብድርና ቁጠባ አገላግሎት የሚሰጡ ተቋማት ናቸው፡፡

6) «ዕድገት ተኮር ስራ ዘርፎች›› ማለት ኢንተርፕራይዞች በዘርፉ ተሰማርተው ቀጣይ እድገት በሚያስመዘግቡበት ለኢንዱስትሪ ልማት መሠረት የሆኑ የስራ ዘርፎች ሲሆኑ ይሄውም የማኒፋክቸሪንግ፣ የኮንስትራክሽንና የከተማ ግብርና የስራ መስኮችን የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ ፕሮጀክት ከ2005 ጀምሮ በአምስት አመታት ውስጥ ተግባራዊ የሚደረግ ሆኖ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ መንግስት አወቃቀር ሥር ለሚገኙ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች፣ እንዲሁም ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአዳማ፣ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህር ዳር፣ ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክለላዊ መንግስት በአዋሳ፣ ለትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በመቀሌ እና የአከካባቢ ከተሞች ነዋሪ በሆኑ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ባለቤቶች በሆኑ ሴቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. <u>ዓላማ</u>

የሴቶች ኢንተርፕሪነርሽፕ ልማት ፕሮጀክት ከፌደራል እስከ አንድ ማእከል አገልግሎት ድረስ ለውጤት በሚበቃ መልኩ ለመፈጸም የሚያስችል የተደራጀና የተቀናጀ ድጋፍና አመራር በመስጠት የተጠቃሚዎችን ገቢና ክህሎት ማሳደግ ነው፡፡

5. <u>የፕሮጀክቱ አስፈላጊነት</u>

ሴቶች በምርትና አገልግሎት ያላቸውን ዝቅተኛ ተሳተፎ ለማሳደግና ለሴት ኢንተርፕሪነሮች ማነቆ ሆነው የቆዩትን የገንዘብ ዕጥረትና የክህሎት ችግሮችን ለመፍታትና ክፍተቱን ለመሙላት የብድር አገልግሎትና ሥልጠና በመስጠት የተጠቃሚዎችን ገቢና የስራ እድል በመፍጠር በኩል ሐገራዊ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የፕሮጀክቱ የወደፊት አቅጣጫዎችና ተጠቃሚዎች</u>

6. <u>የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች</u>

የፕሮጀክት ተጠቃሚዎች ከላይ በተጠቀሱት ከተሞችና አካባቢ የሚገኙ የሴት ኢንተርፕራይዞች ሆነው፣

ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል (51% ያላነሰ ድርሻ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተፕራይዝ ባለንብት የሆኑ ሴት ኢንተርፕሪነሮች ፣

2) አብዛኛውን ጊዜያቸውን በሥራቸው ላይ የሚያሳልፉና፤የሙሉ ቀን ተማሪ ያልሆኑ
3) ኢንተርፕራይዞቻቸውን ለማሳደግ ከፍተኛ ፍላጎትና ብቃት ያላቸው ሴቶች ናቸው።

7. <u>የፕሮጀክቱ የትኩረት አቅጣጫ</u>

1) የሴቶች ኢንተርፕረነርሽፕ ልማት ፕሮጀክት የሴት ኢንተርፕረነሮችን ገቢና የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅም ለማሳደግ የብድር አገልግሎት፣ የኢንዱስትሪ ኤክስተንሽን፣ የሥራ ፈጠራ ክህሎት፣ የቴክኖሎጂ ልማት እና የክላስተር አገልግሎት ድጋፎችን ይሠጣል።
2) በፕሮጀክቱ የሚሳተፉ በዚህ መመርያ አንቀጽ 10 (1-8) የተጠቀሱት አነስተኛ የብድርና ቁጠባ ተቋማት ለፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ሴቶች የብድር አገልገሎት ይሰጣሉ። በሂደትም መስፈርቱን የሚያሟሉ ተጨማሪ አበዳሪ ተቋማት የሚካተቱበት ሁኔታ ይኖራል።
3) የብድርና ቁጠባ ተቋማት ሠራተኞች በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ ምርጥ ተሞክሮዎችንና የብድር ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙና ፖሊሲዎቻቸውንና አሠራራቸውን ይበልጥ እንዲያሻሽሉ የቴክኒክ ድጋፍና ሥልጠና ይሰጣቸዋል።
4) ሴት ኢንተርፕረነሮች በአራቱም ፓኬጆች የክህሎት ሥልጠናዎችና የኢንዱስትሪ ኤክስተንሽን ድጋፍን ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች እንዲያገኙ ይደረጋል።
5) ዓለማቀፍ ተሞክሮን ያካተተ ሥርዓተ ትምህርትና የሥልጠና ሞጁሎች በአማካሪ ድርጅት ተዘጋጅተው ለተመረጡት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች መምሕራን የአሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል፤
6) በቀጣይ ሴት ተጠቃሚዎች የአሠልጣኞች ሥልጠና በመሰዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ መምሕራን የስልጠና ፍላጎታቸውንና የሙያና ክህሎት ክፍተታቸውን መሠረት ያደረገ ሥልጠና ይሰጣል።
7) ሴት ተጠቃሚዎች የንግድ ሥራቸውን በቅንጅት በመሥራት የአንድነት አቅማቸውንና የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲጠቀሙ በአካባቢዎቻቸው መሰባሰብ (ክላስተር) ድጋፍ ለሚፈልጉ አገልግሎቶች ዝግጅት የሚስችል ጥናት ይከናወናል።

የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
The Federal Democratic ... Development

9. <u>የአንድ ማዕከል አገልግሎት፡-</u>

በስድስቱም ከተሞች የተመረጡ 45 የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች ወደ መርሐ-ግብሩ የመግቢያ በሮች ሆነው የተመረጡ ሲሆን፤ የማእከላቱ አመራረጥ በማእከልነት ለሌሎች ማእከላት ያላቸው ቀረቤታ፤የቢሮ አመቺነት፤የሰው ሐይል መሟልትና ፕሮጀክቱን ለመተግበር ያለው ዝግጁነት ናቸው።

ስለሆነም ተጠቃሚዎች በነዚሁ ማእከላት ተመዝግበውና መታወቅያ አግኝተው ወደ ቀጣይ አገልግሎቶች ይመራሉ ። የአንድ ማእከል አገልግሎት ጽ/በቶቹ የኢኮኖሚ መሠረተ ልማትአቅርቦትን በተለይ ለህጋዊ ተቋማት መንግሥታዊ ድጋፎችን በተሟላ መልኩ የመስጠትና ተከታትሎ የማስፈጸም ስራ ያከናውናሉ።

የማእከለቱ ዝርዝርም እንደሚከተለው ነው።

| ተ.ቁ | ከተማ | ክፍለ ከተማ | ወረዳ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|
| ሀ) | አዲስ አበባ | አዲስ ከተማ | ወረዳ 07 እና 08 | |
| | | አራዳ | ወረዳ 02 እና 08 | |
| | | አቃቂ ቃሊቲ | ወረዳ 03 እና 07 | |
| | | ቦሌ | ወረዳ 07 እና 13 | |
| | | ጉለሌ | ወረዳ 03 እና 07 | |
| | | ልደታ | ወረዳ 01 እና 03 | |
| | | ኮልፌ ቀራንዮ | ወረዳ 05 እና 10 | |
| | | ቂርቆስ | ወረዳ 02 እና 05 | |
| | | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | ወረዳ 06 እና 11 | |
| | | የካ | ወረዳ 06 እና 08 | |
| ለ) | አዳማ | | | ቀበሌ 04 |
| | | | | ቀበሌ 07 |
| | | | | ቀበሌ 08 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | ቀበሌ 09 |
| | | | | ቀበሌ 12 |
| ሐ) | ባህርዳር | | | ቀበሌ 01 |
| | | | | ቀበሌ 02 |
| | | | | ቀበሌ 03 |
| | | | | ቀበሌ 05 |
| | | | | ቀበሌ 06 |
| መ) | ድሬ ዳዋ | | | ቀበሌ 02 |
| | | | | ቀበሌ 04 |
| | | | | ቀበሌ 05 |
| | | | | ቀበሌ 07 |
| | | | | ቀበሌ 09 |
| ሠ) | ሀዋሳ | ሀይቅ ዳር | | |
| | | መሃል ከተማ | | |
| | | መንሀሪያ | | |
| | | ታቦር | | |
| | | አዲስ ከተማ | | |
| ረ) | መቀሌ | ቀዳማይ ወያነ | | |
| | | ሓወልቲ | | |
| | | ዓይደር | | |
| | | ሰሜን | | |
| | | ዓዲ ሓቂ | | |

10. አነስተኛ የብድርና ቁጠባ ተቋማት፡

በፕሮጀክቱ የቆይታ ጊዜ ሌሎች ብቃቱ ያላቸው ተመሳሳይ የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ አገልግሎት ሰጪዎች ሳትፎ እንደተጠበቀ ሆኖ፤በአሁኑ ወቅት በመርሐ ግብሩ ስምንት አነስተኛ የብድርና ቁጠባ ተቋማት የሚሳተፉ ሲሆን እነዚህም፡-

1) አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም፣
2) አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም፣
3) ኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ አክሲዮን ማኅበር፣
4) ኦሞ ብድርና ቁጠባ ተቋም፣
5) ደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም፣
6) ልዩ የገንዘብና የእገዛ ተቋም፣
7) ዋሳሳ ብድርና ቁጠባ ተቋም እና
8) ሀርቡ ማይክሮ ፋይናንስ ኢ.ማ ሲሆኑ፣

እነዚህ አነስተኛ የብድርና ቁጠባ ተቋማት የኢትዮጵያ ልማት ባንክና የዓለም ባንክ በተስማሙበት ኦፕረሽናል ማንዋል መሰረት የሚሰሩ ሆኖ፤ለፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ሴቶች ባላቸው የብድር ፖሊሲና መመሪያ መሠረት የብድር አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

ተቋማቱ ሐገራዊ የዘርፉን ስትራተጂ በተከተለ የአገልግሎት ትኩረታቸው በእድገት ተኮር የስራ ዘርፎችና አምራች ኢንተርፕራይዞች ላይ እንዲሆን፤የዘመናዊ ማምረቻ መሳርያ ባለቤት በማድረግ በኩል ሚና እንዲኖራቸው ይበረታታሉ፡፡

11. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች፡

በስድስቱም ከተሞች የሚገኙ 11 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች ከአንድ ማዕከል አገልግሎቶች ጋር መረጃ በመለዋወጥ የሴት ኢንተርፕረነሮችን አቅም በመገንባት በኩል ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ ይህም በመሆኑ ገበያ የሚፈልገውን ምርትና አገልግሎትን በብዛትና በጥራት ለማቅረብና ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን ወሳኝ የሆኑትን

የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማትን መሠረት ያደረገ የጥራትና ምርታማነት፣የቴክኒክ ክህሎት፣የቴክኖሎጂ አቅምና የሥራ ፈጣሪነት ክህሎት በመፍጠር በኩል አይነተኛ ሚና የጫወታሉ። ይህም ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ሆኖ ለሥልጠና በተዘጋጁት ፓኬጆች መሠረት ይከናወናል።

ከዚህም ጋር በተጓዳኝ በውጭ አማካሪዎች ድጋፍ በሚዘጋጁት የሥልጠና ሞጁሎች አማካኝነት ፍላጎትና ክፍተትን መሰረት ያደረጉ ሥልጠናዎች ለሴት ተጠቃሚዎች ይሰጣሉ። የሥልጠና ማእከላቱም የሚከተሉት ኖቸው፡-

1) በክልል ደረጃ

ሀ) የመቀሌ ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ፣

ለ) የባህር ዳር ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ፣

ሐ) የአዳማ ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ፣

መ) የሐዋሳ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ናቸው

2) ከአዲስ አበባ ፣

ሀ) ምስራቅ ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ፣

ለ) እንጦጦ ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ፣

ሐ) ተግባረዕድ ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ፣

መ) ጀኔራል ዊንጌት ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ፣

ሠ) ንፋስ ስልክ ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ እና

ረ) አቃቂ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ናቸው።

3) ከድሬዳዋ

የመለስ ዜናዊ መታሰቢያ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ

## ክፍል አራት

## የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

12. የከተማ ልማት፤ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

የፕሮጀክቱ ባለቤት በመሆን እንዲመራና ሌሎች ሚኒስቴር መ/ቤቶችን በማስተባበር የማስፈጸም ኃላፊነት ከመንግስት የተቀበለ ሲሆን ይህንን ኃላፊነቱን በመወጣት በኩል ተጠሪነቱ ለዚህ ሚ/መ/ቤት የሆነውና በሥሩ የተደራጀው የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ በኩል ያስፈጽማል፡፡

13. የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ፡-

1. አጠቃላይ የፕሮጀክቱን አተገባበር በፌዴራል፣ በክልል፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ያሉ ፈጻሚዎችን ይከታተላል፤
2. የፌዴራል ቴ/ሙ/ት ሥልጠና ኤጀንሲንና የኢትዮጵያ ልማት ባንክን ያስተባብራል፣
3. የፕሮጀክት ማነጅሜንት፣ የፕሮጀክት አድቮከሲና ተደራሽነት እንዲሁም ክትትልና ግምገማ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

14. የክልል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮዎች/ኤጀንሲዎች፡-

የከተሞቹን ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤቶች ማስተባበር፣ መረጃ የመ ቀበል፤የመከታተልና ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡በምርት ሥራ ለሚሰማሩና የመሬትና የመሳርያ ሊዝን አገልግሎት ጥያቄ ለሚያቀርቡ ብቁ ሴት ኢኒተርፕረነሮች ጥያቅያቸው ምላሽ እንዲያገኝ ያደርጋል

15. የከተሞቹ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤቶች፡-

1. የአንድ ማዕከል አገልግሎቶችን ድጋፍ የማስተባበር፣
2. ተጠቃሚዎች ችግሮች ሲያጋጥሟቸው የመፍታት፣
3. ድጋፍ የመስጠትና የመከታተል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

16. <u>የሴቶች፣ የሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፡-</u>

1. የፕሮጀክቱን ሥራ የሚደግፍ ባለሙያ የመመደብ፣
2. ለአድቮከሲና ተደራሽነት ግብአት የመስጠትና ከፕሮጀክቱ ሠራተኞች ጋር በመተባበር የአድቮከሲና ተደራሽነት ስትራቴጂ በማዘጋጀት፣ በክልል ቢሮዎችና በከተማ ጽ/ቤቶች እንዲሁም በወረዳዎች የፕሮግራሙን ተደራሽነት የመከታተልና የማረጋገጥ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

17. <u>የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ፡</u>

1. ከፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር በተመረጡት ከተሞች የሚገኙት የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ሴት ኢንተርፕረነሮች ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች ተገቢ ሥልጠና እንዲያገኙ የሚያስችል መረሀ ግብር ያዘጋጃል፤በመርሀ ግብሩ መሰረት መከናወኑን ያረጋግጣል፡፡
2. ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ባላቸው አሰልጣኞች በሚዘጋጁ የሥልጠና ሞጁሎች የኮሌጆቹ መምህራን በአሰልጣኞች ሥልጠና ዘዴ እንዲሠለጥኑና አቅማቸው እንዲገነባ ያስተባብራል ፤አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

18. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች ሴት ኢንተርፕረነሮች ያለባቸውን የጥራትና ምርታማነት ክፍተት፤የቴክኒክ ክህሎት እንዲሁም የቴክኖሎጂና የስራ ፈጣሪነት አቅም በመገንባት በኩል ችግር ፈቺ ሥልጠና መስጠታቸውንና ማብቃታቸውን እንዲሁም ኮሌጆቹን የመደገፍና የመከታተል ኃላፊነት አለበት፡፡

19.<u>የክልል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ፡</u>

የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲና የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ በጋራ ለኮሎጆቹ የሚያዘጋጁትን የሴት ኢንተረፕረነሮች የስልጠናና የአቅም ግንባታ መርሀ ግብር በክልሉ ያስፈጽማል፡፡ከክልሉ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀኒሲ ጋር የፕሮግራሙን አፈጻጸም ይከታተላል፡፡

20. <u>የኢትዮጵያ ልማት ባንክ፡-</u>

1. በባንኩ የፕሮጀክት ቡድን ማቋቋም፣
2. የአሰራር መመሪያ ማዘጋጀት፣
3. ፕሮጀክቱን የመከታተልና፣ የማስፈጸም፣
4. የአነስተኛ የብድርና ቁጠባ ተቋማትን መረጃ ማሰባሰብና ሪፖርት ማቅረብ፣
5. ለአነስተኛ የብድርና ቁጠባ ተቋማት ብድር የመሥጠት፣ አፈጻጸሙን የመከታተልና የመገምገም እንዲሁም ስለፕሮጀክቱ አፈጻጸም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና ለፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ሪፖሪት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡

21..የአንድ ማእከል አገልግሎት

1. ማእከላቱ ሴት ኢንተርፕሪነሮችን የመመዝገብ፣ መታወቂያ የመስጠት፣ የአገልግሎት መስፈርቶችን በማስገንዘብ ፣ብድርና ሥልጠና የሚያገኙባቸውን መንገዶች መምራትና መሰል ድጋፎችን ይሰጣሉ፣

2. ከዚህም በተጨማሪ የዚህ ፕሮጀክት ተጠቃሚ የሆኑ የሴት ኢንተርፕራይዞችን ሕጋዊነት ለማስፈጎና ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር አንጻር የሚሰጡ ሌሎች አገልግሎቶችንና መንግሥታዊ ድጋፎችን በተቀናጀ መልኩ በአንድ ሥፍራ የሚያገኙበትና ተጠቃሚ የሚሆኑበት መንገድ ያመቻቻል፡፡

3. በእድገት ተኮር የሥራ ዘርፎች በተለይም በምርት ሥራ ላይ ተሠማሩ አምራች ኢንተርፕራይዞችና ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ገበያ ትስስር ለፈጠሩት ተቋማት የተለየ ትኩረት በመስጠት ያበረታታል፡፡

* በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development Housing & Construction

## ክፍል አምስት

## የሚጠበቅ ውጤት

22. ከፕሮጀክቱ የሚጠበቅ ውጤት

1. ከሴቶች ኢንተርፕሪነርሽፕ ልማት ፕሮጀክት የሚጠበቀው ውጤት በስድስቱም ከተሞች በፕሮጀክቱ የብድር አገልግሎትና ሥልጠና ተጠቃሚ የሆኑ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በሴቶች ባለንብረትነት የተያዙ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ገቢና የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅም ያድጋል፡፡

2. ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ለአምስት ዓመታት በመተግበር ላይ ባለው በዚህ ፕሮጀክት ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ የተመለከቱ ሦስት ተግባራት (Components) የሚከናወን ሲሆን፤

ሀ. በእነዚህም ተግባራት የብድር፣ የቴክኒክ ድጋፍ፣ የሥራ ፈጠራ ክህሎት፣ የቴክኖሎጂ ልማት እና የክላስተር ድጋፍ ይሠጣል፡፡

ለ. በእድገት ተኮር የሥራ ዘርፎች የተሰማሩ አምራች ኢንተርፕራይዞች እንዲበረታቱ ይደረጋል

ሐ. ፕሮጀክቱ በሚተገበርባቸው ከተሞች በሚሰጡ አገልግሎቶች 20000 (ሃያ ሺህ) ሴቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

| | ተግባራት (Component) | ንዑስ ተግባራት (Sub-Components) |
|---|---|---|
| 1) | የፋይናንስ አቅርቦት ተደራሽነት (Access to Microfinance) | ብድር (Credit Facility)<br>የቴክኒክ ድጋፍ (Technical Assistance Facility to MFI's) |
| 2) | የኢንተርፕሪነርሽፕ ክህሎት፣ ቴክኖሎጂና የስብስብ (ክላስተር) | የኢንተርፕሪነርሽፕና ቴክኖሎጂ ልማት (Entrepreneurship and technology |

1) የስቲሪንግ ኮሚቴ (Steering Committee) የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

የሴቶች ኢንተርፕሪነርሽፕ ልማት ፕሮጀክት በሥራ ላይ ያሉትን ሴት ኢንተርፕሪነሮችን በብድርና በሥልጠና በመደገፍ ገቢያቸውን እንዲያሳድጉ፣ ክህሎቶቻቸውን እንዲያዳብሩና የሥራ ዕድል ፈጣሪ እንዲሆኑ ለማስቻል የሚያደርገው ጥረት ስኬታማ እንዲሆን፣ ፕሮጀክቱ የበርካታ መ/ቤቶችን ድጋፍና ትብብር የሚጠይቅ ሀገራዊ የልማት እንቅስቃሴ አካል በመሆኑ ስቲሪንግ ኮሚቴው የሚከተለውን ያከናውናል፡፡

ሀ) አስፈጻሚ መ/ቤቶች በፕሮጀክቱ አፈጻጸም ላይ ወቅታዊና የተቀናጀ ድጋፍ መስጠታቸውን ይከታተላል፣

ለ) ፕሮጀክቱ በእቅዱ መሠረት እያከናወነ መሆኑን፣ ማከናወኑንና መፈጸሙን ይገመግማል፣ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣አቅጣጫም ያስቀምጣል፣

ሐ) የክልል ባለድረሻ አካላት ፕሮጀክቱን በተመለከተ ድርሻቸውን እንዲወጡ ያስተባብራል .

መ) የፕሮጀክቱን ቅልጥፍናና ውጤታማነት ለማረጋገጥ በከፍተኛ ደረጃ ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት ውሳኔ ይሰጣል፣

ሠ) የስብሰባ ጊዜውን በስድስት ወር አንድ ጊዜ ያካሂዳል፣ይሁንና ፕሮጀክቱ እስኪጠናከር ድረስ በ3 ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡ ይህም ስብሰባ ከፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ም/ቤት ቀደም ብሎ የሚካሄድ ሲሆን፣ እንደአስፈላጊነቱም አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

2) የስቲሪንግ ኮሚቴ አባላት (Steering Committee)

ሀ) የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር - ሰብሳቢ

ለ) የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስተራክሽን ሚኒስቴር የከተማ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አባል

ሐ) የትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ - አባል

መ) የሴቶች፣ ሕጻናት ... ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ - አባል

ሠ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ም/ገገር - አባል

ረ) የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዝዳንት - አባል

ሰ) የኢትዮጵያ የብድርና ቁጠባ ተቋማት ማኅበር ኤክስኩቲቭ ዳይሬክተር - አባል

ሸ) የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር- አባልና ፀሐፊ

ቀ) የአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋምና የኦሮምያ የብድርና ቁጠባ ተቋም ያለ ድምጽ ተሳታፊ አባላት፡፡

3) አስተግባሪ ኮሚቴ (Operational Committee) የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

የአስተግባሪ ኮሚቴ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

ሀ) በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የተዘጋጀው ዓመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም ይከታተላል ያማክራል፤ድጋፍ ይሰጣል

ለ) የተጠቃሚዎችን ግንዛቤ ለማሳደግ በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ እገዛ ያደርጋል፣ ይሳተፋል፣

ሐ) በኮሚቴ አባል መ/ቤቶችና ተቋማት የሚከናወኑ የፕሮጀክቱ ተግባራት በወቅቱና በአግባቡ መከናወናቸውን ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፣

መ) የፕሮጀክቱ ተግባራት (Components) በሚመለከታቸው ፈጻሚ አካላት በኩል መፈጸማቸውን፣ የክትትልና ግምገማ ስራዎች በወቅቱ መከናወኑንና ስራዎች እየተሳለጡ መሆኑን ይከታተላል፤ በችግሮች አፈታት ይሳተፋል፣ ያማክራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣

ሠ) ለክልሎች መሰጠት ያለባቸው ድጋፎችና አገልግሎቶች፣ በወቅቱ መሰጠታቸውን፣ ሴት ኢንተርፕረነሮች ተጠቃሚ መሆናቸንና ውጤት ማስገኘታቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣

ረ) ከአንድ ማዕከል አገልግሎት ጀምሮ ያሉት አስፈጻሚዎች ተገቢና ተከታታይነት ያለው መረጃ መያዛቸውንና መረጃው ጥቅም ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣

ሰ) የፕሮጀክቱን ወቅታዊ ሪፖርቶች ይመለከታል፣ይከታተላል፣ አፈጻጸማቸውን ይገመግማል አስተያየት ይሰጣል፣

ሸ) ሥራዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ መሠረት እየተከናወኑ መሆኑን ይከታተላል ላጋጠሙ ችግሮች በመፍትሄ አሰጣጥ ላይ እገዛ ያደርጋል ያማክራል፣

ቀ) በየሁለት ወሩ አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ የሚኖረው ሲሆን እንዳስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

በ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የቴክኒክ ኮሚቴ በማቋቋም ጥናቶች፣የመስክ ግምገማዎች፣ የተሞክሮ ቅመራዎች እንዲከናወኑ ሊያደርግ ይችላል።

ተ) የአስተባባሪ ኮሚቴ አባላት የፕሮጀክቱ አስፈጻሚና የአጋር መ/ቤት አባላት ይሆናሉ።

25.. የአስተግባሪ ኮሚቴ (Operational Committee) አባላት

ሀ) የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ዳይሬክተር ሰብሳቢ

ለ) የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ም/ዋ/ዳይሬክተር----ም/ሰብሳቢ

ሐ) የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ የኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አባል

መ) የሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የሴቶችና ወጣቶች አደረጃጀት ድጋፍና ክትትል ባለሙያ-አባል

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development Housing & Construction

ሠ) የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የውጭ ንግድ፣ ብድር ዋስትና እና የስፔሻል ፈንድ አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ-አባል

ረ) በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የአነስተኛ ፋይናንስ ሱፐርቪዥን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር-አባል

ሰ) የኢትዮጵያ የብድርና ቁጠባ ተቋማት ማኅበር ባለሙያ - አባል

ሸ) የሴቶች ኢንተርፕሪነርሽፕ ልማት ፕሮጀክት አስተባባሪ- ጸሐፊና አባል

26.የስብሰባ ቦታ

ሀ) ስቲሪንግ ኮሚቴ (Steering Committee) አባላት የስብሰባ ቦታ በከተማ ልማት፣ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ይሆናል፣

ለ) አስተግባሪ ኮሚቴ (Operational Committee) አባላት በፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የውጤት መለኪያዎች

27. የፕሮጀክቱ ውጤት መለኪያ ዋነኛ መስፈርቶች

የፕሮጀክቱን ውጤት ለመለካት የሚከተሉት ዋነኛ መስፈርቶች በጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

1) የአጭር ጊዜ ስኬት ፋይዳ መለኪያዎች

ሀ) ለተበዳሪዎች የተከፋፈለ የብድር ገንዘብ መጠን፤

ለ) የፕሮጀክት ብድር ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች ብዛት፤

ሐ) የፕሮጀክት ተጠቃሚዎች ከ3 ወር (90 ቀን) በላይ ያልተከፈለ የብድር መጠን፤

መ) በፕሮጀክቱ የሰለጠኑ የብድርና ቁጠባ ተቋማት ባለሙያዎች ብዛት፤

ሠ) በንግድ ወይም በቴክኒክ ሙያ የሰለጠኑ የፕሮጀክት ተጠቃሚ ሴቶች ብዛት፤

ረ) በፕሮጀክቱ አገልግሎት ላይ የተሰማሩ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ባለሙያዎች

ብዛት፣

ሰ) በፕሮጀክቱ አገልግሎት ላይ የተሠማሩና ሥልጠና ያገኙ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ባለሙያዎች ብዛት፣

2) የረጂም ጊዜ ስኬት ፋይዳ መለኪያዎች

ሀ) የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች አማካይ ዓመታዊ ገቢ ዕድገት፣

ለ) የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች የፈጠሩት ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል፣

ሐ) የኢንተርፕራይዞቹ ዕለታዊ/ሳምንታዊ/ወይም ወርሀዊ የሥራ ሰዓት እድገት

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

28. መመሪያውን ስለማሻሻል:-

ይህን መመሪያ ማሻሻል ሲያስፈልግ በማንኛውም ጊዜ በስትሪን ኮሚቴው ሊሻሻል ይችላል::

29. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ:

ይህ መመሪያ ከዛሬ ሚያዝያ 1 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ይሆናል::

መኩሪያ ኃይሌ ተክለማርያም

የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

ሚኒስትር